# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 50

ጥር 21 ቀን 2015 ዓም(21-01-2023)

የዚህን ሳምንታዊ አገር ሰነበተች ጥንቅራችንን የምንጀምረው ባለፈው የሳምንቱ መጨረሻ እሁድ ቀን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዙሪያ በመንግሥታዊ ሴራ ታጅቦ የተከሰተውን ቀውስ በማስቀደም ይሆናል።በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ላይ የታወጀው ዘመቻ ከሳምንቱ ወዲህ የተጠነሰሰ ሳይሆን ዓመታትን ያስቆጠረ ፣እያደገ የመጣና ከዚህ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው።ቤተ ክርስቲያኗ ይህንን ፈተና ገና ከጅምሩ አንስታ ስትጋፈጠው ኖራለች።ወያኔና ኦነግ ከጫካ ጀምረው ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲነሱ ዒላማ (ታርጌት) ያደረጉት ለአገራዊ አንድነቱ መሰረትና ምሰሶ በሆኑት በሁለቱ ማለትም በቤተክርስቲያኗና በአማራው ተወላጅ ላይ ነው። ኦርቶዶክስ እምነት የአማራው ብቻ ሳትሆን የትግሬው፣የኦሮሞው፣የከንባታው፣የሃድያው የጉራጌው፣የሲዳማው፣ የወላይታው፣የገሙው፣የሽናሹ፣የአገው፣የቅማንቱ፣የጋምቤላው---ወዘተ መሆኗን ባለፈው የጥምቀት በዓል አከባበር በተረዱት ነበር። አማራ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ብቻ አይደለም።የአማራ ሙስሊም፣የአማራ ፕሮቴስታንትና ካቶሊክ የሌላውም እምነት ተከታዮች ያቀፈ ማህበረሰብ ነው። ኢትዮጵያም እንዲሁ የተለያዩ ጎሳዎች የሚኖሩባት፣የተለያዩ እምነቶች የሚስተናገዱባት አገር ነች።ይህንን ገሃድ ሃቅ የማይቀበሉና የከዱ ለፖለቲካ ሥልጣንና ጥቅም የቋመጡ ከሌላው አልፈው በራሳቸው ጎሳ ተወላጆች ላይ ሳይቀር የጥፋት ካራ መዘዋል።ወያኔዎቹም አከርካሪውን ሰብረነዋል ሲሉ የራሳቸውንም ጎሳ ተወላጅ ጭምር የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት መሠረት የሆነውን የትግራይን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጀው እንደሆነ የትግራይ ሕዝብ ሊረዳ ይገባዋል።የኦሮሞም ተወላጅ እንዲሁ ኦነግም እንደ ወያኔዎቹ የማይራራላቸው መሆኑን በእምነታቸው የተነሳ ከሚያርዳቸው ንፁሃን ኦሮሞዎች ሊማር ያገባዋል። እነዚህ ሁለቱና በስራቸው የሚርመሰመሱት የጥፋት ሃይሎች ሃይማኖትም አገራዊ ስሜትም የሌላቸው እዬዘረፉ ለመኖር የሚሹ የባዕዳን ተላላኪዎች ናቸው እንጂ ለተወለዱበት ማህበረሰብ አስበውና ተጨንቀው ለዲሞክራሲና ፍትሕ መስፈን፣ለአገራዊ አንድነትና የሕዝብ አብሮነት የሚታገሉ አይደሉም። ስለነዚህ የጥፋት ሃይሎች ብዙ ጊዜ እየተከታተልን ሥራቸውንም ያጋለጥንና የተቃወምን በመሆኑ የሰሞኑ ድርጊታቸው ለእኛ አዲስ ክስተት አይደለም።ወዴት እንደሚያመራ ካካሄዳቸው ተነስተን ለማሳዬት ሞክረናል።

ከሁለት ዓመት ወዲህ ወያኔ ትግራይን ገንጥዬ አገር እሆናለሁ ብሎ ባሰበበት ጊዜ በትግራይ ውስጥ ያለውን የቤተክርስቲያኗን አካል ገንጥሎ ፓትሪያርክ መሾሙና ጳጳሳት ሾሞ ከግብጽ እውቅና ጠይቆ እንደነበር ይታወቃል።አሁንም ያ ቡድን በይፋ መፍረሱ አልታወቀም፤ይቅርታ ጠይቆ መመለሱም አልተገለጸም።ያ ማለት በተጠባባቂነት አድፍጦ ተቀምጧል ማለት ነው።ይህም የኦነጋውያን የሰሞኑ የጳጳሶች ሲመት የዛው የወያኔዎቹ ተከታይ አገር የማፍረስ እንቅስቃሴ አካል ነው።በጣም የሚገርመው ለጵጵስና ቀርቶ ለቅስና ብቃት የሌላቸውን ከዬመንገዱ ለቃቅሞ ጳጳስ ማድረጉ በራሱ የኦሮሞን ሕዝበ ክርስቲያን መናቅ ነው።ወይም ለኦሮሞ ኦርቶዶክሳዊ ዲያቆን መች አነሰው የማለት ያህል ነው።

ቤተክርስቲያናችን እንደማንኛውም ተቋም ድክመት ሊኖርባት ይችላል።ድክመቷን በአንድነት እዬተማከሩ ይፈቷል እንጂ ለመፍታት ባይቻል እንኳን ለዬአድባራቱ መሪዎችና ምዕመናን ችግሩን ይገልጻሉ እንጂ ከእምነት መመሪያ ሕግና ሥርዓት ውጭ በሆነ መልኩ በስከጀርባ አድማ ጠንስሶ፣ካባና ቆብ አሰፍቶ፣እራስን ጳጳስና ፓትሪያርክ ብሎ በመሰዬም ለመገንጠል ምክንያት አይሆንም።ብዙ መከራና ፈተናዎችን አልፋለች

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባለፈችበት አያሌ ዘመናት ብዙ ፈተናዎችንና ችግሮችን አለፋለች፤በግራኝ ሞሃመድ፣በዮዲት ጉዲት፣በአውሮፓ ካቶሎኮች፣በቅባቶች፣በደርግ አምባገነኖች፣በወያኔ፣የሚደርስባትን ፈተና ተቋቁማ አሁን ካለችበት የኦነጋውያን ጊዜ ላይ ደርሳለች። የአሁኑን የተለዬ የሚያደርገው ግን ከውጭ የመጣባት ችግር ብቻ ሳይሆን ከውስጧ ባፈነገጡ ልጆቿ ጭምር ያጋጠማት ችግርና ፈተና ነው።ይህ በውስጥና በውጭ ጠላቶቿ እንዲሁም ሥልጣኑን በያዘ ቡድንና መንግሥታዊ ተቋም ጋር የተሳሰረ መሆኑ ችግሩን ውስብስብና የተለዬ ያደርገዋል። ሆኖም ግን ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን አሁንም የሚደርስባትን ፈተና በሃይማኖት አባቶችና በምእመናኑ ጽናትና ትግል ማለፏ አይቀርም። የኦነጋውያኑ አፈንጋጭ ጳጳሳት ውንጀላና ለመገንጠል ምክንያት ያደረጉት ቤተክርስቲያኗ በአንድ ጎሳ ተጽእኖ ሥር ወድቃ ትምህርቱና ሰበካው በአንድ ቋንቋ ማለትም በአማርኛ ብቻ ሆኖ ለሁሉም ጎሳ የእምነቱ ተከታይ ተደራሽ አልሆነም የሚል ሰበብ በመጠቀም ነው።እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እነሱን እራሳቸውን ጨምሮ ሌሎችም የማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑ ጳጳሳትና ቀሳውስት እንዳሉና ትምህርተ ሰበካውም በተለያዩ ቋንቋዎች እንደሚሰጥ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ መፈለግ አያስፈልግም።ሌላው ተልካሻ ምክንያታቸው ደግሞ የጳጳሳቱ ስም በኦሮሞ ስም አለመሰዬሙ ነው የሚል ነው።በመጀመሪያ ደረጃ የጳጳሳቶች ስም አወጣጥ ከቀደምት ሃዋርያት ስም ጋር የተያያዘ ሆኖ በግብርም የሃዋርያቱን ሥራ እንዲገልጹ የሚያሳስብ ነው።ያፈነገጡትም ቢሆኑ በዛው መጠሪያ ሲጠሩ ኖረዋል፤ያሁኑም የፍንገላው የኦነጋውያን ፓትሪያርክ ተብዬ የተሰጠው ስም የሐዋርያቱን የተከተለ እንጂ የኦሮሞ ስም አይደለም። ለመሆኑ ኦሮሞ የሚል አገርና ማህበረሰብ የት የነበረና የታወቀ ሆኖ ነው የሐዋርያቱን ስም ሊተካ የሚችለው?ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ ይሏል እንዲህ አይነቱን እብደት ነው።ሌላው ደግሞ መvዘ,ፍቅዱስ በአማርኛ ብቻ ተጽፏል የሚል ነው።

የጦስ ዶሮ ይመስል ሁሉም የሚወነጅለው አማራ በአማርኛ በመጽሓፍ ቅዱስ አገልግሎት ካገኘ ከሰባ ዓመት አይበልጠውም ።ከዚያ በፊት እንደሁሉም ያገሪቱ ዜጋ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ የሚከታተለው የመጽሓፍ ቅዱስ ትምህርት በግዕዝ ቋንቋየተጻፈውን ነበር። ታዲያ ከዬት መጥቶ ነው የአማራው ሃይማኖት ነው የሚባለው?እንደታሪኩማ ከሆነ የክርስትና እምነትን በመጀመሪያ የተቀበሉት የኢትዮጵያ ንጉሶች ከትግራይ መሬት ላይ የበቀሉት አብርሃና አጽብሃ ነበሩ።ለዚያም ነው ግእዝን ተመራጭ ያደረገው።ቤተክርሲያኗ ባላት አቅም ሁሉንም ጎሳ ለመድረስ ሞክራለች። ከጋምቤላ እስከ ባሌና ሞያሌ፣ከጅግጅጋ እስከወለጋ ጉሙዝና ቤኒሻንጉል፣ከከፋ እስከ ጋሞና ሲዳማ፣ከአፋር እስከ ጅቡቲ ድረስ ያሉትን የተለያዩ ቋንቋ በሚናገሩት ማህበረሰቦች ውስጥ ገብታ በቋንቋቸው ለማስተማር ሞክራለች፣ከዛም አልፎ ተርፎ በአፍሪካ ፣በአውሮፓ፣በአሜሪካ፣በመካከለኛው ምስራቅ፣አገሮች በምትችለው አቅም እምነቱን አስተምራለች፣አገልግሎትም ሰጥታለች።ካላት ውስን፣ ግብአት(ሪሶርስና)ላለፉት 50 ዓመት በሰፈኑት ጸረ ሕዝብና ጸረ ሃይማኖት ከሆኑት መንግሥታቱ ጫና የተነሳ ያሰበችውንና የምትመኘውን ሙሉ ለሙሉ በተግባር ልትተረጉመው አልቻለችም።በዬቦታው ሰባኪያኑ፣ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ በግፍ ታርደውባታል፤ቤተክርስቲያናትም በእሳት ጋይተዋል፤ንብረቷ ተዘርፏል ወድሟል፤ምዕመናኑም ተጨፍጭፈዋል።በሁሉም ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም አቅም ቢኖራት የምታደርገው በግእዙ ፊደሏ እንጂ በላቲን ፊደል እንደማይሆን መታወቅ ይኖርበታል።ያ የባዕዳንን የበላይነት አምኖ ባርነትን ፈቅዶ የመቀበል ውሳኔ ማለት ይሆናል።

በዬገጠሩ ፊደል በማስቆጠሩ፣ዕርዳታ በመስጠቱ ደረጃም የማይናቅ ሚና ተጫውታለች። በፊትና አሁን በሥልጣን ላይ ያሉትን ፊደል አስቆጥራ ከመሃይምነት ያወጣችው ይህችው ጠላት አድርገው የተነሱባት ቤተክህነት ናት። መንግሥት ነኝ ብሎ የትምህርት ግብር ከሚሰበስበው መንግሥት ተብዬ ዘራፊ ቡድን በተሻለ መልኩ በባዶ እግር ተጉዘው በየገጠሩ ማህይምነትን የተዋጉ ቀሳውስትን አስማርታ የምትችለውን አድርጋለች፤ በማድረግም ላይ ነች።

የሰሞኑ የተከሰተው የፓትሪያርክና የሲኖዶስ ፍንገላ ሙከራ የተጠራቀመው አገር የመበታተን ሴራ ዳር ላይ መድረሱን ያመለክታል። በቀናት ውስጥ ተወጥኖ ያደገ ነው የሚል ግምት የለንም።አድፍጦ ጊዜ ጠብቆ የመጣ ድርጊት ነው።የጥምቀት አከባበሩ ን በማዬት ተስፋ የመቁረጥ እርምጃም እንደሆነ እንረዳለን።በአንድ ሳምንት ውስጥ የታቀደ አለመሆኑ ከአቀራረቡ መረዳት የሚቻል ሲሆን ከወራት በፊትም በዬአድባራቱ ያሉትን ጳጳሳትና መነኮሳት ለማጥመድ እንቅስቃሴ እንደነበር አሻፈረን ካሉት አባቶች በኩል የሚሰጠው ማስረጃ ያረጋግጣል። የግብጽ ኦርቶዶክስ እውቅና እንዲሰጥ ተጠይቆም እምቢ እንዳለ ተሰምቷል።ይህ ግን የግብጾችን አቋም ከማዬት አንጻር ለነገው ዋስትና ይሆናል ማለት አይደለም።

የኦነጋውያኑ እንቅስቃሴ ከወያኔው ሙከራ ጋር ተናቦ የሚሠራ እንቅስቃሴ እንጂ ብቻውን የሚንቀሳቀስ አይደለም።የሁለቱም ዓላማ ኢትዮጵያን የመበታተን ዓላማ ነው።ስለሆነም ይህ አገር አፍራሽና ሕዝብ አጫራሽ ሙከራ እንዳይሳካ ማድረግ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ብቻ ሳይሆን ሁሉም አገር ወዳድ የመኖር ያለመኖር ጥያቄ መሆኑን ሊረዳ ይገባል።ስለሆነም ሙስሊሙ፣ፕሮቴስታንቱም፣ካቶሊኩም ከቤተ ክርስቲያኗ ጎን ሊቆም ይገባዋል።ትናንትና በሙስሊሙ ላይ ፣ዛሬ በኦርቶዶክስ ላይ የተደረገው ድፍረት ነገ በካቶሊኩና በአገር ወዳዶቹ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ላይ ላለመደረጉ ዋስትና የለም።ሰሞኑን በሙስሊሙ መጅሊስ የወጣው መግለጫ ለአንድነቱ ማስረጃ የጎሰኞቹን ጥጋብ ማብረጃ እንደሚሆን አንጠራጠርም።ሕዝብ በሁሉም አቅጣጫ ሲተባበር የጠላት ጉልበቱ እዬዛለ ይሄዳል፤ በመጨረሻም ተንበርክኮ ይወድቃል።

ከሥርዓቱ ጋር የተሳሰረ መሆኑን የሚያሳዬውና የሚያረጋግጠው ሌላው

1. የመንግሥት ባለሥልጣኖች የመከላከያ ሚኒስቴሩ አብርሃም፣የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ሃላፊው ጥሩነህ ተመስገንና ሌሎቹ በመንበረ ፓትሪያርኩ ግቢ ገብተው በድፍረት ያስተላለፉት ማስጠንቀቂያና ዛቻ ነው።

2. እውር ዝምብ ለይቼ አውቃለሁ ብሎ የሚመጻደቀው የደህንነቱ ቢሮ ከተማ ለከተማ እዬዞረ በሃይማኖት ከለላ ተደራጅቶ በዬሆቴሉ አድማ የሚመታውን የኦነግ መንጋ በዝምታ ማለፉ የሴራው አካልነቱን በግልጽ ያሳያል።

3. ለተገንጣዩ የኦነጋውያኑ ሕገወጥ ሲኖዶስ የጥበቃ፣የገንዘብና የመረጃ ድጋፍ ሲያደርግ በሕጋዊው የሲኖዶሱ ግቢ ለዓመታት በቋሚነት ተመድቦ የነበረውን የጥበቃ ክፍል ከቦታው ማንሳቱ ፓትሪያርኩንና ሌሎቹን ጳጳሳት ለአደጋ የተጋለጡ ለማድረግ ነው።
4. የኦነጋውያኑ መሪ የሆነው አብይ አህመድ በበኩሉ የፕሮቴስታንቱን እምነት ጠልፎ የኦርቶዶክስ ተዋህዶን ለማፍረስ መሣሪያ ለማድረግ የሄደበት መንገድ የወርቅ ሰንሰለት ሸልሞ በላከው ፓስተር ዮናታን በሚባለው መደዴ በኩል የተረጨው መርዝ ማስረጃ ነው።ነብይ ነኝ ብሎ የሚቀደደው ዮናታን ከሱ ያነሱትን የማስተዋል ችሎታ የሌላቸውን ድውያን ሰብስቦ ተአምር ተገለጠልኝ በማለት ያሳዬው ድራማ ሌላው የፕሮቴስታንትን እምነት ያዋረደ እንጂ ያስከበረ ድርጊት አይደለም። የፕሮስታንት እምነት ምንጭና ባለቤት በሆኑት አውሮፓውያን ዘንድ እንዲህ አይነት ማጭበርበርና እብደት በፍጹም ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።በአገራችን ግን

አባይ ጠንቋይና አወናባጅ በነብይ ስም ያሻውን እያደረገ ይገኛል።ዮናታን ከጠንቋዩ ከእያንጓለለው ብርሃኑ የሚለይበት ቢኖር በፕሮቴስታንት ስም መነገዱና በሥርዓቱ መታቀፉ ነው።ዮናታን የፈጣሪ መልእክተኛ ሳይሆን የኦነግ መራሹ የአብይ አህመድ ሥርዓት ተላላኪ ነው።የኢ,ጋውያኑን አገር የማፍረስ ሴራ በሃይማኖት ስም የሚያስፈጽም ከንቱ እራስ ወዳድ ነው።ይህንን ከንቱ ሰው ከቦ የሚያጨበጭብና ሃሌ ሉያ እያለ የሚጮህ የማስተዋል ችሎታ የሌለው ለጥፋት የተሰለፈ ጅላጅል ብቻ ነው።በቀና መንፈስ ተታለው ተከታይ የሆኑ ቢኖሩ ሁኔታውን ተገንዝበው እራሳቸውን ከጥፋት ጉዞ አውጥተው የእምነት ቤታቸውን አጽድተው፤ ለአገራቸውና ለወገናቸው ብቻም ሳይሆን ለራሳቸው ሰላምና እምነት ሲሉ የኦነጋውያኑን ሴራ ሊያወግዙት ይገባል።

5 በሕዝቡ ግብር የተቋቋሙት የመንግሥት የዜና አውታሮች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶና በሕዝቡ ላይ ያንዣበበውን አደጋና የአደጋውን ጠንሳሾች በሚመለከት ምንም አይነት ዜና አለማቅረቡ ብቻም ሳይሆን አልፎ ተርፎም ሰላም ወረደ፣እዚህ ቦታ ይህ ፕሮጀክት ተመረቀ በሚል ጫጫታ እውነቱን መሸፈኑ የሴራው ባለቤት አብይ አህመድ የሚመራው ቡድን መሆኑን ያረጋግጣል።

6 አንዳንድ የመንግሥት አካላት የኦነጋውያኑ የጳጳሳት ጎራ ከመሸገበት ሆቴል ወጥቶ ለመደራደር ያቀረበውን ጥያቄ በሰላም ስም መደገፋቸውም የሴራው አካልነታቸውን በግልጽ ያሳያል።

7 ለቤተክርስቲያን ምረቃ ወደ ጅማ ያቀኑትን የከባቢውን ሊቃነ ጳጳስ አቡነ እስጢፋኖስንና የሰንበት ትምህርት ቤት ሃላፊ የሆኑትን ከአፄር ማረፊያ በወታደር አስገድዶ እንዲመለሱ ያደረገው አብይ አህመድ የሚመራው የኦነግ መራሹ አህዴድ አስተዳደር ነው።

ይህ ሁሉ መከራና ግፊት ባለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ አባላት ከዬቦታው ተሰባስበው በሁኔታው ላይ ለመወያዬት በወሰኑት መሠረት ሁሉም ተገኝተው ቆፍጠን ያለ ውሳኔ አሳልፈዋል።ካሳለፉት ውሳኔ ውስጥ ከሃድያኑ ከማንኛውም የቤተክርስቲያን አገልግሎት መታገዳቸው፣ከድቁና እስከ ጵጵስና የነበራቸውን ሹመትና ምዕረግ እንዲሁም ስያሜ ተገፈው ወላጆቻቸው ባወጡላቸው ዓለማዊ ስማቸው እንዲጠሩ ወስኗል።ይህንን ውሳኔ በአገር ውስጥና በውጭ ያሉ የቤተክርስቲያኗ አገልጋዮች፣ማህበረ ሰበካዎችና ምዕመናን፣የውጭ አገራት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ጭምር በመደገፍ ከሃዲያኑን አውግዘዋል።ቤተክርስቲያን የይቅርታ ተምሳሌት መሆኗ ቢታወቅም የጠፋው በግ ተመልሶ መጣ በሚል ሰበብ ያለምንም ስነሥርዓታዊና ቀኖናዊ ሕጋዊ እርምጃ ማለፍ አይኖርባትም።

አንዱ ኮብላይ በፈጸመው ክህደት ተጸጽቶ ይቅርታ ጠይቆ በመመለሱ ከነበረው ክብርና ቦታ ወርዶ አቶ ተብሎ ተራ ምድራዊ ሕይወቱን እንዲመራ ተፈቅዶለታል። ሌሎቹም ይህንን ፈለግ እንዲከተሉ ጥሪ ተደርጎላቸዋል።በዚህ የተደናገጠው አፈንጋጮቹ ቡድን ከኦነጋውያን ጋር በመሆን በያዘው መንገድ እንደሚቀጥል የገለጸ ሲሆን በወለጋና በሌሎቹ ቦታዎች በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ በአማርኛ እንዳይቀደስ፣እንዳይሰበክ ብቻም ሳይሆን ኦሮሞ ያልሆነ የእምነት አባትና ምዕመን ዝር እንዳይል መከልከሉን አሳውቋል።የፓትሪያርኩንም ስያሜ ይፋ አድርጓል።

ከዚያም አልፎ ተርፎ መግለጫ አውጥቷል።የመግለጫው ይዘት ልዩነቱን የብሔር ብሔረሰቦች አድርጎ ሕዝብ ለሕዝብ ለማባላት የተሄደበት መንገድ ከኦነግያውያኑ የፖለቲካ ቡድኖችጋር ሙሉ ለሙሉ

የሚመሳሰል ነው።እነሱ እራሳቸው በኦሮሞነታቸው ሳይገፉ ጳጳስ ሆነው ያገለገሉባትን ቤተክርስቲያን በጸረ ኦሮሞነት መክሰሳቸው በሥልጣን ላይ ያሉትን ከሃዲ የኦሮሞ ተወላጆችን ፈለግ የተከተለ ነው። እነሱም እንደ አነጋውያን ፖለቲከኞች በሆነው ባልሆነው ውሸትና ተራ ውንጀላ የታጀበው የክህደት መግለጫ ኢትዮጵያን በመበታተን የጎሰኞች አገራዊ ምሥረታ መንደርደሪያ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ከጳጳስ ቀርቶ ከአንድ ሰካራም የማይጠበቅ ቅጥፈትና ክህደት፣የሕዝብ እልቂትን የሚቀሰቅስ ሰይጣናዊ ተልእኮ መግለጫ ጥቁር ካባ ለብሶ የኦነግ አሸባሪ ቡድን ያቀረበው እንጂ የሃይማኖት አባቶች አቋም ነው አንልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህወሃትና ኦነግ በሚቆጣጠሩት የመንግሥት ሃይል ጋር ተባብረው በሁሉም አቅጫጫ የከፈቱበትን የእልቂት ዘመቻ በአንድነትና በጽናት ሊታገለውና ሊያሸንፈው ይገባል።በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሃይማኖትና ጎሳ ሳይለዩው የመጣበትን የጋራ ጠላት በሚችለው ሁሉ እንዲታገለው፣ከአገር ቤቱ ሕዝባዊ ትግል ጋር በቅንጅት እንዲሠራ ጥሪ እናደርጋለን። በዬሚኖርበት አገር ላሉት የሃይማኖት ተቋማትና መንግሥታት ሊከሰት የሚችለውን ቀውስ በማስረዳት ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጎን እንዲቆሙ መጠዬቅ ይገባዋል።

ከቤተክርስቲያኗ ወጣ ስንል በሳምንቱ የታዘብነው ሌላው ጉዳይ

አገር በዚህ አደገኛ ቀውስ ውስጥ በገባችበት ጊዜ አብይ አህመድ ወደ ካርቱም መሄዱና የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ ከወረረው አምባገነን ጀነራል አልቡርሃን ጋር መተቃቀፉ ምናልባትም በወልቃይት በኩል ያለውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ለመግታት የሱዳን ወታደራዊ ሃይል እንዲተባበር ለመጠዬቅ ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አድሮብናል።ያንንም እውን የሚያደርገው የተነጋገረው ምን እንደሆነ ይፋ አለመሆኑ ነው።

የኦነግ አሸባሪ ቡድን በሥርዓቱ እዬታገዘ በአማራው ተወላጅ ላይ የሚያደርገውን ጭፍጨፋና የቤተክርስቲያን ውድመት በስፋት ቀጥሎበታልው።በወለጋ ያለው ሁኔታ ካለፈው የተለዬ አይደለም። ከዛም ወጣ ብሎ በሰሜን ሸዋ የኦነግ እንቅስቃሴ ተስፋፍቷል።በሰምበቴ፣በማጀቴ፣በአጣዬ ፣በሸዋ እሮቢት ወረራና ጭፍጨፋው ተጠናክሯል።ንብረት ወድሟል፣ተዘርፏል።ከሞት የተረፈው ሕዝብ የፈናቅሎ ለችግር ተጋልጦ የእርዳታ ያለህ እያለ ይጮሃል። መንግሥት ተብዬው ቡድን ያገሪቱን ገንዘብ በዳንኪራና በፓርክ ሥራ ያባክናል።ኢትዮጵያን እያፈረሰ ኦሮሚያ የተባለች አገር በመገንባት ላይ ተጠምዷል።ወያኔም እንዲሁ ትግራይን ገንጥሎ ለመሄድ ውስጥ ውስጡን በማመቻቸት ላይ ነው።

አገራችን በሁሉም ዘርፍ በቀውስ ማዕበል እዬተናጠች ትገኛለች። የፖለቲካው ቀውስ ፣የገንዘብ ግሽበቱ፣ የጤናና የትምህርት ዘርፉ መናጋት፣የምርት እጥረቱ፣የበሽታው፣የድህነቱ፣የመፈናቀሉ፣የሰላም እጦቱ፣ የሙስናና ዘረፋው መስፋፋት ፣የኑሮ ውድነቱ ተደራርቦ አገራችንን ወደ ባሰ ትርምስና የእርስ በርስ እልቂት እንዳይከታት ያሰጋል።ሰሞኑን የወጣው የተማሪዎች ውጤት የሚያሳዬው ከላይ የጠቀስነውን የትምህርት ተቋም መናጋት በተጨባጭ ማስረጃ,ሚያረጋግጥ ነው።በተሰጠው መግለጫከ900 ሺህ ተማሪ 29 ሺህ ብቻ ማለፉ፣ ከዚያም 1500 ትምህርት ቤቶች ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ካቀረቧቸው ውስጥ አንድም ተማሪ አለማለፉ የውድቀታችን ማሳያ ነው።

ከሚያስፈራው አደጋ ለመዳን ያለው ብቸኛ መንገድ ለመከራዎች ሁሉ ያጋለጠንን የጎሰኞች ሥርዓት መቀዬር ብቻ ነው።

በእስልምና ሂይማኖት ና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የተቃጣውን የማጥፋት ዘመቻ፣በአማራውና በአገር ወዳዱ ማህበረሰብ ተወላጅ ላይ የሚደርሰውን ጭፍጨፋና ማፈናቀል እዬተቃወምን ለግፉአን ድምጻቸውን ከሚያሰሙት ጋር መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን።

በመጨረሻ ላይ ልናስተላልፍ የምንወደው መልእክት ሥርዓቱ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ችግሮችን እዬጎተተ ለማዘናጋት የሚጠቀምበትን መንገድ ተረድተን ሳንዘናጋ በነበረው አቋማችን ጸንተን እንድንቆም ለማሳሰብ ሲሆን በግፍ ያሠራቸውን ወገኖቻችንን ሳንረሳ ፍትሕ እንዲያገኙ የምንጠይቀውን ጥያቄ አሁንም  በአጽንኦት እንድንቀጥልበት ነው።በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው፣አዛውንቱ ታዲዎስ ታንቱ በጨካኞች እጅ ላይ ወድቆ በስቃይ ላይ እንደሚገኝ ተገንዝበን ፍትሕ ለታዲዎስ እያልን ከጎኑ እንድንቆም ጥሪ እናደርጋለን።

ፍትሕ ለታዲዎስ ታንቱ!

የጎሰኞች ሴራ ይከሽፋል፤ኢትዮጵያም በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!